<u>ተምታቶብኛል</u>
<u>የቱን ጨብጬ የቱን ልተወው</u>

ታዛቢው ከለንደን

በኢትዮጵያ በቅርቡ የሚካሄደውን አገር አቀፍ ብሔራዊ አጠቃላይ ምርጫን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ መንግስት፣ ከገዥው ፓርቲ፣ ከተቃዋሚ ፓርቲዎችና ድርጅቶች፣ እንዲሁም የአገራቸው ጉዳይ ከሚመለከታቸው ቡድኖችና ግለሰቦች የተለያዩ ሀሳቦች ሲሰነዘሩ ቆይተዋል::

ምርጫውን አስመልክቶ በገዥው ፓርቲና ራሳቸውን እንደተቃዋሚ ፓርቲ ባስመዘገቡ የተወሰኑ ፓርቲዎች መካከል ውይይትና ድርድር ተደርጎበት ስምምነት ላይ የተደረሰበት "<u>የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ</u> <u>የስነምግባር ደንብ</u>" የፓርቲ መሪዎቹ ተፈራርመውበት ይፋ ከወጣ በህዋላ ውይይቱ ጦፍዋል ፅሁፎችም በየድህረ-ገፁ እየቀረቡ ናቸው:: ተራ ዘለፋውንና አሽሙሩን ሳንቆጥር ማለቴ ነው!!

እኔ ብዙም ፖለቲካ አላውቅም:: ማንበብና መፃፍ እችላለሁ :: አንድ ነገር ግልፅ ሆኖ ከቀረበልኝ ይገባኛል ብዬ አምናለሁ::ብሳሳት አደራችሁን ይቅር ብላችሁ ቅፅል ስም ሳትሰጡኝ በአግባቡ አስተምሩኝ::

እንደተረዳሁት ከየአቅጣጫው የሚሰነዘሩት ሃሳቦች ዋና ፍሬ ነገር፣

**አንደኛው ወገን-** በኢትዮጵያ ውስጥ 'አንቱ' የተባለ የአገሪቱ ሕገ-መንግስት አለ:: ይሁንና ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ ራሱ አርቅቆ- ተወያይቶ- አፅድቆ ያወጣውን የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ይህንን ሕገ-መንግስት በማያከብርበት፣የምርጫ አስፈፃሚው አካል ገለልተኛ ባልሆነበት፣በመላው አገሪቱ የሚገኘው የመከላከያ- የፖሊስና የፀጥታ ሃይል ሙሉ በሙሉ በኢህአዴግ ቁጥጥር ስር ባለበት፣ፍርድ ቤቶች ነፃ ባልሆኑበት፣ የፕሬስ ነፃነት በሌለበት ሁኔታ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ማካሄድ በፍፁም አይቻልም::
ኢሕአዴግ የክልል ምርጫዎችን ከ99% በላይ ባሸነፈበት መልኩ ይህንንም ብሄራዊ ምርጫ እንዲያሸንፍ ተደርጎ በሚዘጋጀው የይስሙላ ምርጫ ላይ መሳተፍ ለኢሕአዴግ እውቅና ከማስገኘት በቀር እውነተኛ ዲሞክራሲ በአገሪቱ ውስጥ አያመጣም::
ኢሕአዴግ-ወያኔ ስልጣን ያሳበደውና ስልጣን መልቀቅ የማይፈልግ የአምባገነን መንግስት ነው፣ ይህንንም ባህርይውን ባለፈው የ2005 ብሔራዊ ምርጫ ላይ አይተነዋል::
ስለሆነም በቅድሚያ መፍትሄ ሊያገኙ ይገባቸዋል የሚባሉ ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው::( ባለ ስንት ነጥብ እንደሆነ ትዝ አይለኝም)
አለበለዚያ በምርጫው ላይ አንሳተፍም :: በማናቸውም የትግል አማራጮች ኢሕአዴግን ታግለን ከስልጣን እናስወግዳለን የሚል ወገን ነው ::

**ሁለተኛው ወገን-** "የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ የስነምግባር ደንብ"ን የፈረሙት ኢሕአዴግን ተቃዋሚ ነን ባይ ፓርቲዎች ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኘውን

የይስሙላም ይሁን የእውነት ጠባብ ዲሞክራሲያዊ መብት ሁሉ በመጠቀም፣ ከመንግስትና ከገዢው ፓርቲ የሚሰነዘረውን ጥቃት በሙሉ በመመከት፣ ማንኛውንም ህጋዊ መንገድ እየተጠቀምን፣ ከአገር ውጭ ሆነን ሳይሆን ህዝቡ አጠገብ ሆነን፣ ህዝቡ የሚደርስበትን ግፍ አብረን እየተጋራን ታግለን እናታግላለን በምርጫውም ላይ እንሳተፋለን ::
አህአዴግን ባዘጋጀው የራሱ ሜዳ ላይ ለትግል እንገጥመዋለን:: መመኪያችንና መሳሪያችን የሆነው ሰፊው ህዝብ ከኛ ጋር ነው:: ይህም ሃይል የኢሕአዴግን የመከላከያ-የፖሊስና የፀጥታ ሃይል ይመክታል፣ ባይ ነው ::

**ሶስተኛው ወገን** - ይህን የምርጫ የስነምግባር ደንብ መፈረሙ ዋጋ የለውም ባይና አንኳር የሆኑ የሚያነጋግሩ ጉደዮች ስላሉ በመጀመሪያ ከኢሕአዴግ ጋር የሁለትዮሽ ውይይት ለማድረግ ጠይቆ አዎንታዊ ምላሽ ያላገኘው "መድረክ" ነው ::
"መድረክ ከተቋቋመ ጀምሮ በኢትዮጵያ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲካሄድ እየሰራ ነው::አሁንም ገዢው ፓርቲ በሚያደርስበት ግፍና የማጥላላት ዘመቻ ተሸንፎ ከምርጫው ሂደት ራሱን አያገልም":: በቅርቡ ከመድረክ ከተሰጠ መግለጫ የተወሰደ::
ይህ አባባል በምርጫው እንሳተፋለን የሚል እንደምታ ያለው ይመስላል

**አራተኛው ወገን** ደግሞ የኔ አይነቱ የትኛውን ጨብጦ የትኛውን እንደሚለቅ ውሉ ጠፍቶበት ማንን እንደሚደግፍ ተቸግሮ ዝም ብሎ ቁጭ ያለ ነው::

እነዚህ ከላይ የቀረቡት አቅዎሞች አራተኛውን ትቶ የሰከነ ውይይት የሚጠይቁ ናቸው:: አንደኛውን አቅዋምም ከመያዝ በፊት ለመንደርደሪያ ያህል ከ2005 ምርጫ በህዋላ የተፈጠረውን በትንሹ መመልከት የሚያስፈልግ ይመስለኛል::

1. የተቃማሚው ክፍል
   - ቅንጅት የ2005 ብሄራዊ ምርጫን ያሸነፈ በመሆኑ ኢ.ህአዴግ ስልጣኑን እንዲለቅ በቆራጥነት አቅዋሙን ቢገልፅም የገዥው ፓርቲ አሻፈረኝ በማለቱ፣ ለድርድር ያቀረባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ኢ.ህአዴግ ከተቀበለ አሸንፏል የተባለባቸውን መቀመጫዎች ይዞ ፓርላማ እንደሚገባ ፍቃደኝነት ቢያሳይም ኢ.ህአዴግ እምቢተኛ በመሆኑ ቅንጅት ፓርላማ አልገባም ብሎ ወሰነ:: (መቼም ፓርላማ አንገባም ተብሎ እንዴት እነደተወሰነ ግንቦት 1998 የታተመውን የዶ/ር ብርሃኑ ነጋን 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' የተሰኘውን መፅሃፍ ከገፅ 165-173 እንዲሁም 'ቅንጅት ከየት ወዴት' በሚል ርእስ በቅንጅት ዋና አስተባባሪ-የምክር ቤቱና የሥራ አስፈፃሚው ቃለጉባዬዎች ያዥና ፀሃፊ በአቶ ገብረክርስቶስ ሐይለስላሴ የተፃፈውን መፅሀፍ ከገፅ 165-173 አንብቡና ወይ እዘኑ አለበለዚያም ልክ ነበር በሉ ::)
   - የህዝብ ቁጣ ገንፍሎ በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች የህዝብ አመፅ ሲነሳ ኢ.ህአዴግ የጥፋት በትሩን ሰነዘረ :: የሰው ህይወት ጠፋ ንብረት ወደመ ብዙሃን ንፁሃን ታሰሩ ::
   - የቅንጅት ከፍተኛ የአመራር አባላት ፓርላማ የገቡትን ትቶ ምክንያት ተፈልጎላቸው አብዛኛዎቻቸው እንዳለ ዘብጥያ ወረዱ:: ቅንጅት እንደ

ድርጅት እንኳን የተገኘውን ድል ማስጠበቅና ህዝቡን መምራት ቀርቶ የራሱን ህልውናም መከላከልና አመራሩን ማዳን የኢህአዴግንም የጥፋት በትር መመከት አቃተው::

- ሁሉ ነገር ቀረና ትግሉ እስረኛ ወደማስፈታት ጉዳይ ላይ አተኮረ::ሰላማዊ ሰልፍ ረሃብ አድማ ህዝባዊ ስብሰባ ዲፕሎማሲያዊ ስራዎች በየቦታው ተደረጉ::
- የቅንጅት የአመራር አካላት የውስጥ ለውስጥ ሽኩቻ ቀስ በቀስ አደባባይ እየወጣ መጣ:: ኢህአዴግ ባሰኘውና በተመቸው ሰአት (ልሳሳት እችላለሁ እስረኞቹን ለማስፈታት በተደረገው ትግል አይመስለኝም) በአማላጅ ሽማግሌዎች አደራዳሪነት መሪዎቹ ከእስር ከተፈቱ በህዋላ በሚያሳዝንና በሚያሳፍር ሁኔታ በግልፅ መዘላለፍ-መሰዳደብ-መናቆር ተያዘ::በዚህም ኢህአዴግ ሊያጠፋው የጀመረውን ድርጅት የራሱ አመራር አካላት ገድለው ቀበሩት::
- ዲያስፖራ ያለው ተቃዋሚ በሙሉ በተለያዩ የቀድሞ የቅንጅት አመራሮች በፈጠሩዋቸው ጎራዎች ውስጥ በቀራጥነት እየዘለለ በመግባት እሳቱን አቀጣጠለው፣ ደም የማይታይበት መጨፋጨፍም አካሄደ ::አብዮት ልጆችዋን በላች-አጣጣመች!!! እንደምጠረጥረው ይሄ ውጭ ከሚኖረው ፖለቲከኛ ውስጥ አንዳንዱ ልበል አብዛኛው እዚያው አገር ቤት ከተማሪዎች ንቅናቄ ጀምሮ ደርግ መኢሶንንና ኢሕአፓን እስከመታበት ጊዜ ድረስ እርስ በራሱ ሲናቆር ሲጠላለፍና ሲገዳደል የነበረና እርስ በራሱም የሚተዋወቅ ይበዛበታል መሰለኝ እኔ አላውቅም ብቻ ምህረት አያውቅም!! ተሳስቻለሁ ብሎ እጅ ማንሰትም የፈጠረበት አይመስለኝም (በፈጠራችሁ በደራሲ ሻ/ል ተስፋዬ ርስቱ የተፃፈውን “ምስክርነት በባለስልጣናቱ አንደበት’ የተሰኘውን መፅሀፍ አንብቡት-ስለ መኢሶንና ኢሕአፓ ማንነት ይገልፅላችሁዋል-እንድታውቁት ያህል ነው:: ታሪኩ እውነትም ሃሰትም ሊሆን ይችላል) ይሄ መቻቻል መደማመጥና በጋራ በሚያስማሙ ጉደዮች ላይ አብሮ መስራት አለመቻል መንስኤው ከያኔው ባህርያችን የመጣ ከሆነ በሚል ፍራቻ ነው ይህን የምለው
- ህዝብ ታዘበ፣አንገቱን ደፍቶ የእለት ኑሮውን ለማሸነፍ ላይ ታች ማለት ጀመረ፣ኢህአዴግ እጎን ቆሞ እኔ አላልኩም? እያለ ተሳለቀ

2. መንግስትና ኢሕአዴግ
   - ትግሉን ካኮላሸሸና የስልጣኑን ርካብ እንደገና ቆንጥጦ ከያዘ በህዋላ የራሱን ድርጅት ጥንካሬና ድክመት መገምገምና ላገዛዝ በሚያመቸው መንገድ ማስተካከል ጀመረ ::
   - ህዝቡን በተለይም የአዲስ አበባን ነዋሪ በተለያየ መንገድ በኑሮ መቅጣት ጀመረ ::
   - የተቃዋሚ ድርጅቶች ስማቸው እንጂ ስራቸው እንዳይታይና እንዳይሰማ ሁሉንም መንገድ ዘጋ-ተሳካለትም
   - የኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች ተስፋፉ ከአገሪቱ ቁልፍ የኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ ሓይሎች አንዱ ሆኑ

- ፍርድ ቤቶችና የህዝብ የመገናኛ ብዙሃን ለመንግስት አደሩ፣ የግሉ ፕሬስ መዋከብ በዛበት-አንዳንዱም እስር ቤት ወረደ ሌላውም እየዘጋ ወደ ሌላ ስራ ገባ
- የመከላከያው ሰራዊት ፖሊስና የፀጥታው ሃይል ለኢህአዴግ እንዲያገለግል ተደርጎ እንደገና ተከረከመ
- ሽብርተኞችን አጠፋለሁ በማለት ሶማሊያን በመውረር በአለም የብቸኛዋን ሃያል አገር አሜሪካ ድጋፍ አገኘ

3. የውጭው ዓለም
   - ምርጫውን አስመልክቶ ኢህአዴግ ውጤቱን እንዳጭበረበረው አንዳንዶች በግልፅ ቅሬታቸውን አሰሙ
   - የደረሰው የህይወትና የንብረት መጥፋት አስቆጣቸው ::
   - ከጥቂት ጊዜ በህዋላ አብዋራው ረገበ:: በየኤምባሲውና በየእርዳታ ሰጪ ድርጅት ውስጥ የሚገኙ መረጃ ሰብሳቢዎች የተቃዋሚው ጎራ ችግር ያለበት መሆኑን መረዳት የሚያቅታቸው አይመስለኝም:: አገሪቱን ለማስተዳደር "ራሱን የቻለ ዝግጁ የሆነ ሃይል የለም" ብለው እንደሆን ኣላውቅም ኢህአዴግን እያባበሉ አብረው ከሱ ጋር መቆየት የመረጡ ይመስላል
   - ለተቃዋሚ ድርጅቶች ጆሮዋቸውን ቢሰጡም ይህ ነው የተባለ ጫና በመንግስት ላይ ሲያደርጉ አይታይም :: ይልቁንም ለአገሪቱ የሚሰጡትን እርዳታ ከአመት አመት ጨምረዋል:: የአገሪቱን የኢኮኖም እድገት በቅንነት ተቀብለው አድንቀዋል :: አቶ መለስን ከብዙዎቹ የአፍሪካ መሪዎች መካከል እንደ አዋቂና ጥሩ መሪ አድርገው ያይዋቸዋል:: የአፍሪካ መሪዎች በተለያዩ አለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ አህጉሪቱን ወክለው እንዲገኙ መርጠዋቸዋል::

ከላይ የዘረዘርኳቸውን አጭር ዋና ዋና ነጥቦች ብንመለከት ከምርጫ 2005 አመት በህዋላ ቅንጅት ፓርላማ አልገባም ብሎ ሲወስን የአገሪቱን የፖለቲካ መድረክ ኢህአዴግ በብቸኝነት እየመራው፣ድጋሚ ተመሳሳይ ስህተት ላለመፈፀም የተንቀሳቀሰበት፣ በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው መስክ በይበልጥ ራሱን ያጠናከረበት፣ በአለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ስራዎችን በመስራት ለጋሽ አገሮች አመለካከታቸው የለዘበ እንዲሆን ያደረገበት ጊዜ ነው :: ይህም ሆኖ ኢህአዴግ ከስልጣን ሊወርድ የማይችል ድርጅት ነው ማለት አይደለም::

በተፃራሪው ደግሞ አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአለፉት አራት አመታት ውስጥ እንቅስቃሴያቸው ተኮላሽቶ፣ ከህዋላቸው ሊከተላቸው የተዘጋጀውን ህዝብ ቀርቶ ራሳቸውን እንኳን እንደገና በአዲስ መልክ ለማደራጀት ጊዜ ወስዶባቸውና ተቸግረው ደፋ ቀና ሲሉ ሌላው ምርጫ ከች ያለባቸው መሆኑን እናያለን :: አንድን ነገር ከሌለ ነገር ጋር አታካፍል አትበሉኝና ፓርላማ ሳይገቡ ውጭ ሆነው የሰሩት ስራና ያስገኙት ውጤት፣ ገብተው ቢሆን ኖሮ ይሰሩት ከነበረው ታሳቢ ስራ ጋር ቢነፃፀር የተወሰነው ውሳኔ ሚዛን የሚደፋ አይመስለኝም:: ይልቁንም የፓርቲያቸውን ህልውና ማስጠበቅ፣መንግስት ወደደም ጠላም ተቀበለውም አልተቀበለውም ሃሰባቸውን በግድ የሚያዳምጥበትበት፣ከህዝቡ ጋር በግልፅ የሚገናኙበት፣እንደልብ በመንቀሳቀስ የድርጅት ስራ የሚሰሩበት ሁኔታ..ሌላም ሌላም

ይፈጠርና አሁን በሚደረገው ምርጫ ላይ ከበፊቱ በበለጠ ሁኔታ ተጠናክረው ይቀርቡ ነበር ባይ ነኝ ::

ለዚህም ነው ፓርላማን ረግጦ በመውጣት ከ2005-2009 ድረስ ኢህአዴግን ማነቃነቅ እንዳልተቻለ፣ እውጭ የሚገኘው ታጋይ አገር ቤት ለሚንቀሳቀሰው ተቃዋሚው ክፍል ድጋፍ ከመስጠት ባሻገር መንግስትን ከስልጣን ሊያወርድ የሚችል ሃይል እንዳልሆነ እየታወቀ፣ የውጭው ለጋሽ አገር ትኩስ ዜና ከተራገበ በህዋላ ሁሉም ነገር ሲሰክን 'ለሚቀጥለው ጊዜ' የሚል ባህርይ እንዳለውና ምንም ኢህአዴግን የሚያደርጉት ነገር እንደሌለ እየታወቀ( ኢሳያስንና ሙጋቤንስ ምን አደረጉ?) ቅድመ ሁኔታዎችን ደርድሮ እነዚህ ነጥቦች ካልተሟሉ ምርጫ ላይ አልሳተፍም ብሎ አቋም መያዙ ለመጪው 5 አመታት የሚያመጣው ጥቅም ምን እነደሆነ በግልፅ እንዲገባን ተደርጎ ሊነገረን የሚገባ ይመስለኛል::

ያለንበት ዘመን ዓለም እንደቀድሞው በሁለት ጎራ ተከፍሎ አንዱ ሃያል አገር ጉያ ስር ተወትፎ ገንዘብ-መሳሪያና ጥይት በገፍ የሚገኝበት አይደለም ፤የጎረቤት አገር ድንበር ላይ መጠለያ አግኝቶ የውትድርና ትምህርት እየወሰዱ የሽምቅ ውጊያ ለማድረግ አስቸጋሪ ነው፣ጎረቤት አገሮቻችንም "ከኤርትራ በሰተቀር" ጥያቄም ቢቀርብላቸው በፍፁም ፍቀደኛ አይሆኑም::የአገራችን ዱርና ገደል ውስጥ መሸፈት ይቻላል:: ለዚህ ደግሞ ድርጅት መሰሪያና ገንዘብ የስፈልጋል::ይሄን ሁሉ ሳገናዝብ በአጭር ዓመታት ውስጥ ይህንን እስከአፍንጫው የታጠቀ መንግስት በትጥቅ ትግል መጣል ይቻላል ብዬ ለማመን ያስቸግረኛል::

ለዚህም ነው ተምታቶብኛል የቱን ጨብጬ የቱን ልተወው ያልኩት!!